# ይድረስ ለ ሃገር ወዳድ ኢትዮጵያውያን በሙሉ

## ጉዳዩ ዘመናዊ ቤተ መፃህፍት በመቀሌ ከተማ ስለመገንባት

ባለፉት ጥቂት ሳምንታት በሃገረ ጀርመን የምትገኝ ቱቢንግን የተባለች ከተማ ከኢትዮጵያዊቷ መቀሌ ከተማ ጋር በእህትማማችነት ለመተሳሰር አቅዱ መቀሌም በተቀመጡት መስፈርቶች የበላይነትን ተቀዳጅታ ትስስሩ ፍፃሜ ላይ ሊደርስ ሲል

ፅናት መሰረቱን ያደረገ ሃገራዊ ልማት - መስዋእትነት ያቀራኘው የህዝቦቻችን የጋራ ራእይ ብሩህ ተስፋ ያጀበው ሃገራዊ የህዳሴ ፋና ሲያዩ የዓይን ብሌናቸው የሚቆሮቁራቸው የትምክህተኛነት አሸን ክታብ አጥልቀው የዘርአዊነት ካባ የተጀቦኑ የህዝብ ጠላቶች በደማቅ የድል አጀብ ቀን በቀን እያሸበረቀ በመሄድ ላይ ያለውን ፈጣን የእናት ምድር ኢትዮጵያ ግንባታ ለማደናቀፍ በማለም ቱቢንግን ላይ ባካሄዱት የተቃውሞ ሰልፍ የሁለቱ ከተሞች ትስስር እንዲኮላሽ አድርገዋል::

እንዲህ አይነቱ እኩይ ተግባር ያስቆጣቸው በመላው ዓለም የሚገኙ ሃገር ወዳድ ኢትዮጵያውያን በሌላ በኩል የህዝቦቻችን አንድነት አዲስ ተስፋና ብሩህ ራእይ ህብሩ ላይ በተጎናፀፈው የባንዴራቸው ሰንደቅ ስር ተሰባስበው ዛሬም እንደ ትላንቱ የህዝባዊ ወገንተኛነት ጋሻ አንግበው የአንምበረከክም ልሳነ ዜማ ደግመው ደጋግመው እየዘመሩ ለመቀሌ ከተማ የሚቻላቸውን ያህል ለማድረግ ቆርጠው ተነስተዋል::

ፓልቶክ ፎረም ገዛ ተጋሩ የውይይት መድረክ እያስተባበረው የመቀሌ ከተማ አስተዳደር ጽህፈት ቤት በቅርብ እየተከታተለውና በመላው ዓለም የሚገኙ ሃገር ወዳድ ኢትዮጵያውያን ተቀላቅለው ርብርቦሹን እያደመቁት የሚገኘው ይህን ፕሮጀክት ሓቦ መቀሌ በሚል ስም የሚጠራው ህዝባዊ ርብርብ እስከ አሁን ድረስ በአይነቱ ለየት ያለና ደረጃውን የጠበቀ በግምት ብር 3 ሚልዮን የሚፈጅ ቤተ መፃህፍት በመቀሌ ከተማ ለማሰራት አቅዶ ገና ከጅምሩ ተስፋ የተሞላው አመርቂ ስራ በመስራት ላይ ይገኛል::

በዚህም መሰረት የዚህ ሰናይ ህዝባዊ ተግባር ዓላማ ዳር ላይ እንዲደርስ በሃገር ውስጥና በውጭ ሃገር የሚትገኙ ኢትዮጵያውያን ሁሉ ከፕሮጀክቱ ዓላማ ጎን በመሰለፍ የበኩላችሁን አስተዋፅኦ ታደርጉ ዘንድ የአክብሮት ጥሪያችንን እናቀርባለን::

ለተጨማሪ መረጃ በ projecthabbomekelle@gmail.com ያግኙን

ትላንት - ዛሬ - ነገ - አንምበረከክም